**Saturday, January 25, 2025**

## HMAHAA Members Meeting

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ/ሐረር ጦር አካዴሚ ምሩቃን ማህበር በሰሜን አሜሪካ የሁለት ወር መደበኛ ስብሰባ

ቀን:- ጃንዋሪ 26 ቀን 2025 ዓ.ም  (January 26, 2025)

ቦታው:- ሆሊዴይ ኢን ኤክስፕሬስ ስፕሪንግ ፊልድ (Holiday Inn Express, Springfield, Virginia)

ሰዓት:- 1:00-5:00 ፒ ኤም

በስብሰባው የተገኙ  ሰዎች ጠ/ብዛት:-  49

አባላት ቁጥር..........34

የአባላት ቤተሰብ ቁጥር---15

የስብሰባው አዘጋጅ:- ኮሎኔል ለማ በየነና ወይዘሮ ትርስት አበበ

የዕለቱ ፕሮግራም ቀጺምተከተል:-

አብላጫ አባላት ከተገኙ በሁዋላ ስብሰባው በ1:45 ሰዓት ተጀምሮአል:: ለማህበሩ አባላት የእንኳዋን ደህና መጣችሁ! መልዕክት ከተላለፈ በሁዋላ ጃኑዋሪ 29, 2024 ህይወቱ ላለፈ የአካዳሚው 6ኛ  ኮርስ ምሩቅና ናይጄርያዊ ዜጋ ለነበረው Augustin Azubugo የአንድ ደቂቃ የህሊና ፀሎት ተደርጎአል:: ቀጥሎም የማህበሩ ሊቀ መንበር ኮሎኔል ጋተው ተፈሪ ለአባላቱ አጭር የመግቢያ ንግግር አድርገዋል::

ከምሳ በሁዋላ ለማህበሩ አባላት በቀረቡት ሶስት  አጀንዳ ርዕሶች ላይ አባላት ተወያይተው  የሚከተሉትን ውሳኔዎች አስተላልፈዋል::

የስብሰባው አጃንዳዎችና ውሳኔዎቹ

1- የርክክብ ሪፓርት:-

-በ12/21/2024 አዲሱ ኮሚቴ ከቀድሞ አመራር  ኮሚቴ በማህበሩ ባንክ አካውንት ውስጥ የተቀመጠ መጠኑ= $ 133,128.23  ተረክቦአል:: እንዲሁም በዚሁ ቀን የተለያዩ ዶኩሜንቶቻችንና ንብረቶች  ማለትም አንድ ላፕቶፕ ኮምፕዩተር: አንድ ፎቶ ካሜራና  ሁለት ስፒኬሮችን ተረክቦአል::

-በ01/26/2025  በተደረገው ስብሰባ ከማህበሩ አባላት የተሰበሰበ ወርሃዊ መዋጮ $ 5,725.00  ገቢ ሆኖአል::

-የማህበሩን ገቢና ወጪ አያያዝና በባንክ አካውንት ውስጥ የሚገኘውን ተቀማጭ ገንዘብ መጠን በተመለከተ ከአባላቱ ጥያቄዎች ተነስተው መልስ ከተሰጠና ውይይት ከተደረገ በሁዋላ ሂሳቡ በኦዲተር እንዲጣራ ተወስኖአል። በውጭ ወይስ በውስጥ ኦዲተር ይጣራ የሚለው ጥያቄ ተነስቶ ወደ ፊት በውጭ ኦዲተር እንዲጣራ ሆኖ ለአሁኑ ግን ገንዘብ ያዥ መ/አለቃ አህመድ መሐመድና ሂሳብ ሹም ሻለቃ ተዘራ በዛበህ ካስፈለገም አንድ ሌላ ሰው ተጨምሮ ከሻምበል በዙ ጋር በመሆን ሂሳቡን እንደገና እንዲያጣሩ ተወስኖአል። በተለይም የከፈሉና ያልከፈሉ አባላትን ለይተው እንዲያጣሩ መመሪያ ተሰጥቶአል።

2. የማህበር ስብሰባ ወጪን ስለ መቀነስ:-

የማህበሩ አባላት ይህንን አጀንዳ በስፋት ከተወያዩ በሁዋላ አባላት እንደ አቅማቸው ያዘጋጁ እንጂ ምንም ለውጥ ሳይደረግ በነበረው ሁኔታ ይቀጥል ብለዋል።

3. የአባላት መረጃ ልውውጥ ዘዴን ስለ ማሻሻል:-

በዚህ አጀንዳ ላይ ሰፊ ውይይት ከተደረገ በሁላ የማህበሩን ምስጢር በጠበቀ ሁኔታ የሚሰራ የመገናኛ ዘዴ አስፈላጊ መሆኑ ግንዛቤ ተወስዶ ዋትስአፕና (WhatsApp)የአካዳሚ ዌብሳይትን (Academy Website) እንድንጠቀም ከስምምነት ላይ ተደርሶአል።

የዕለቱ ስብሰባ በ5:00 ፒ ኤም ተጠናቆአል።